## <u>የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሕግ ፡ አወጣጥ ፡ ረገድ ፡ የሚፈጽመው ፡ ተግባር ።</u>

### ከክቡር ፡ አቶ ፡ ሥዩም ፡ ሐረጎት ።*

በዛሬው ፡ ዕለት ፡ ከመሐከላችሁ ፡ ተገኝቼ ፡ "በሕግ ፡ አወጣጥ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ስላለው ተግባር ፡" አጭር ፡ ንግግር ፡ ለማድረግ ፡ በመቻሌ ፡ የተለየ ፡ ደስታ ፡ ይሰማኛል ። ምክንያቱም ፡ ይህ ፡ ታዳጊ ፡ የሆነው ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ባለሙያዎችን ፡ ቁጥር ፡ በየደረጃው ፡ እየጨመረ ፡ እንዲሄድ ፡ ማድረጉን ፡ ስለማውቅ ፡ ከሕግ ፡ ባለሙያዎች ፡ አንዱ ፡ እንደመሆኔ ፡ መጠን ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ ስለፈጸመው ፡ ከፍተኛ፡ ተግባር ፡ የተሰማኝን ፡ ደስታ ፡ ለመግለጽ ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘሁት ፡ ነው።

የሕግ ፡ ሙያ ፡ ለአንድ ፡ አገር ፡ ዕድገትና ፡ ሰላም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ለእናንተ ፡ ለሕግ ፡ ባለሙያዎችና ፡ ደጋፊዎች ፡ መዘርዘር ፡ አያሻም ። ኢትዮጵያ ፡ አገራችን፡ ጥንት ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ጀምሮ ሲያያዝ ፡ የመጣ ፡ የሕግ ፡ እውቀትና ፡ ፍልስፍና ፡ በፍርድ ፡ አጠባበቅም ፡ የረጅም ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ እንዳላት ፡ በሁላችሁም ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ሕዝቡም ፡ የተፈጥሮ ፡ የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ ዝንባሌ ፡ አለው ፡ እየተባለ ፡ እስካሁን ፡ የሚነገርለት ፡ ከዩኒቨርሲቲው ፡ በየጊዜው ፡ እየተመረቁ ፡ በወጡት ፡ የሕግ ፡ ባለሙያዎች ፡ የአዕምሮ ፡ ንቃትና ፡ ችሎታ ፡ ተመስክሮአል ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ ።

ሕግ ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሚፈጽመው ፡ ተግባር ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ከመዘርዘር ፡ በፊት ፡ ራሱ ፡ "ሕግ ፡" የሚለው ፡ ቃል ፡ ምንን ፡ እንደሚያጠቃልል ፡ ባጭሩ ፡ መግለጽ ፡ ተገቢ ፡ ይሆናል ።

፩/ <u>ሕግ ፡ በኢትዮጵያ ፡—</u>

በኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አቋም ፡ "ሕግ ፡" የሚለው ፡ ቃል ፡ የሚከተሉትን ፡ ያጠቃልላል ፡-

1/ <u>አዋጅ</u> ፡- አዋጅ ፡ ማለት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፬ ፡ ፴፮ ፡ እና ፡ ከ፹፰—፺፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የሚፈጸም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ካጠናውና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፓርለማ ፡ ከመከረበት ፡በኋላ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲጸድቅ ፡ የሚወጣ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

2/ <u>ድንጋጌ</u> ፡- ድንጋጌ ፡ ማለት ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ መሠረት ፡ ፓርለማ ፡ ዝግ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ አስቸኳይ ፡ ጉዳይ ፡ ሲያጋጥም ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ከመከረበት ፡ በኋላ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚደነገግ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

3/ <u>ትእዛዝ</u> ፡- ትእዛዝ ፡ ማለት ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከአንቀጽ ፡ ፳፯—፴፮ ፡ እና ፡ በሌሎችም ፡ አንቀጾች ፡ ተዘርዝሮ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡

---

* ይህ ፡ አንቀጽ ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ ሥዩም ፡ ሐረጎት ፤ በጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሚኒስትር ፤ በ፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም. የቀድሞ ፡ ሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ ባዘጋጀው ፡ የምሳ ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ በክብር ፡ እንግዳነት ፡ ባደረጉት ፡ ንግግር ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።

መሠረት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መክሮበት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚወጣ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

4/ ደንብ ፦ ደንብ ፡ ማለትም ፡ አንድ፤ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ በቻርተር ፡ የተቋቋመ ፡ ድርጅት ፡ በአዋጅ ፡ በድንጋጌ ፡ ወይም ፡ በትእዛዝ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የሚያወጣው ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ያለውን ፡ ተግባር ፡ ከመዘርዘር ፡ በፊት ፡ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ተግባር ፡ የሚያስቡትን ፡ እንመልከት ። በአንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ አስተሳሰብ ፡ ሕግ ፡ ማመንጨትና ፡ ማውጣት ፡ የፓርላማ ፡ ሥራ ፡ ነው፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ደግሞ ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውል ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሕግ ፡ በማውጣት ፡ ረገድ ፡ ምን ፡ ተካፋይነት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ሊሰነዘር ፡ ይቻላል።

እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ታላቅ ፡ የፖለቲካ ፡ አምድ ፡ ሆኖ ፡ ሲሠራበት ፡ የቆየው ፡ የፖለቲካ ፡ ፍልስፍና ፡ የአንድ ፡ መንግሥትን ፡ አቋም ፡ ሶስት ፡ ላይ ፡ መመደቡ ፡ ነው ። በዚህም ፡ "የፖለቲካ ፡ ሥልጣን ፡ አከፋፈል ፡" በተባለው ፡ ፍልስፍና ፡ መሠረት ፡ የአንድ ፡ አገር ፡ የመንግሥት ፡ አቋም ፡ ሶስት ፡ ማዕዘን ፡ አለው ። እነዚህም ፦

ሕግን ፡ የማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ------------------------------ ፓርላማ ፡
ሕግን ፡ የማስፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ --------------- የአስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡
ሕግን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ የመዳኘት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው-----የዳኝነት ፡ ክፍል ፡ ይባላሉ ።

ይህን ፡ መሠረታዊ ፡ የፖለቲካ ፡ ፍልስፍና ፡ መላው ፡ ዓለም ፡ ተቀብሎት ፡ የሚሠራበት ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትም ፡ በዚሁ ፡ ፍልስፍና ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ። ይህ ፡ የፖለቲካ ፡ ፍልስፍና ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ሶስቱ ፡ የመንግሥት ፡ አቋሞች ፡ ማለት ፡ ፓርለማ ፡ የአስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ የዳኝነት ፡ ክፍል ፡ ግንኙነት ፡ ሳይኖራቸው ፡ ተለያይተው ፡ ለየብቻቸው ፡ ተግባራቸውን ፡ መፈጸም ፡ ይችላሉ ፡ የሚል ፡ አለመሆኑ ፡ መታወቅ ፡ ይኖርበታል ። የፍልስፍናውን ፡ መሠረታዊ ፡ አስተሳሰብ ፡ በትክክል ፡ መረዳት ፡ ሲያስፈልግ ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ መደረግ ፡ ያለበትም ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ነው ። የዚህ ፡ የፖለቲካ ፡ ፍልስፍና ፡ ትክክለኛው ፡ ዓላማ ፡ እነዚህ ፡ ሶስት ፡ አቋሞች ፡ ሚዛናቸውን ፡ ጠብቀው ፡ በመተባበር ፡ እንዲሠሩና ፡ አንዱ ፡ የሌላውን ፡ አቋም ፡ ሥልጣን ፡ እንዳያጠቃልል ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲደረግ ፡ የሚያሳስብ ፡ ነው። በሌላም ፡ አነጋገር ፡ ለምሳሌ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ከሌሎቹ ፡ ጋር ፡ ተባብሮ ፡ ሥራውን ፡ በሚፈጽምበት ፡ ወቅት ፡ ሕግ ፡ የማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ ቢኖረውም ፡ የፓርለማን ፡ ሥልጣን ፡ በሙሉ ፡ በመረከብ ፡ ፓርለማን ፡ አስወግዶ ፡ ሕግ ፡ የማውጣትንና ፡ የማስፈጸምን ፡ ሥልጣን ፡ አጠቃልዬ ፡ ለብቻዬ ፡ እሠራለሁ ፡ እንዳይል ፡ እንዲሁም ፡ ፓርለማው ፡ የአስፈጻሚውን ፡ ሥልጣን ፡ ለብቻዬ ፡ እሠራለሁ ፡ እንዳይል ፡ ይከለክላል ። ይህ ፡ ቢፈጸም ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ የፖለቲካ ፡ መሠረታዊ ፡ አስተሳሰብ ፡ ተሻረ ፡ ማለት ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ስለፖለቲካ ፡ ቲዎሪ ፡ የምናወሳውን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ እናብቃና ፡ ዛሬ ፡ ልንነጋገርበት ፡ ወደሰብነው ፡ ጉዳይ ፡ ተመልሰን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሕግ ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጽመው ፡ ተግባር ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ እንመልከት ።

## ፪/ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የሚሰጠው ፡ የሕግ ፡ ማውጣት ፡ ተግባር ፡-

ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ስንመለከት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሕግ ፡ በሚመንጭበትና ፡ በሚታወጅበት ፡ ጊዜ ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባውን ፡ በዝርዝር ፡ የሚያመለክቱ ፡ አንቀጾች ፡ መኖራቸውን ፡ እንረዳለን ። የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፸፮ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይነበባል ፡-

> "ሚኒስትሮች ፡ በጉባኤ ፡ ተነጋግረውባቸው ፡ የወሰኗቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በኩል ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይቀርባሉ ፡ በማንኛዎቹም ፡ ነገሮች ፡ ሕግ ፡ እንዲወጣ ፡ አስፈላጊ ፡ ወይም ፡ የተገባ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መክሮበት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲፈቅዱ ፡ ውሳኔዎቹ ፡ የሕግ ሃሳብ ፡ ሆነው ፡ ለፓርለማ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በኩል ፡ ይላካሉ ፡" ይላል ።

ይህም ፡ አንቀጽ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የወሰናቸው ፡ ጉዳዮች ፡ አዋጅ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ሆነው ፡ ከተገኙ ፡ ለፓርላማ ፡ የሚላከውን ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ራሱ፡ አዘጋጅቶ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የሚፈቅድ ፡ ነው ። ይህ ፡ አባባል ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሕግ ፡ በሚመነጭበት ፡ ጊዜ ፡ ያለውን ፡ ተግባር ፡ ያመለክታል ።

በሕግ ፡ አቀራረብ ፡ በኩል ፡ አንቀጽ ፡ ፸፮ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ የሚኒስትሮችን ፡ ምክር ፡ ቤትና ፡ የፓርለማን ፡ የሥራ ፡ ተባባሪነት ፡ የሚያጠቃልል ፡ ስለሆነ ፡ የሚመለከተው ፡ በተለይ ፡ የአዋጅን ፡ አቀራረብ ፡ ነው [1] ። ይሁንና ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ አዋጅ ፡ ሆኖ ፡ የሚወጣ ፡ ሕግ ፡ በሚዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጭምር ፡ ተሳታፊ ፡ ነው ፡ ቢባልም ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፬ ፡ እና ፡ ፹፯ (ሀ) ፡ መሠረት ፡ ደግሞ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማንኛውንም ፡ አዋጅ ፡ ሆኖ ፡ የሚወጣ ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ አመንጭተው ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሳይመክርበት ፡ የሕጉን ፡ ሃሳብ ፡ በቀጥታ ፡ ለፓርላማ ፡ እንዲላክ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከታወጀበት ፡ ከ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በአሠራር ፡ እንደታየው ፡ አንድም ፡ አዋጅ ፡ በአንቀጽ ፡ ፸፮ ፡ መሠረት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሳይመክርበት ፡ ለፓርለማ ፡ ተልኮ ፡ አያውቅም ።

ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፸፮ ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ከአዋጅ ፡ ሌላ ፡ ድንጋጌንና ፡ ትእዛዝን ፡ ለማመንጨት ፡ ስልጣን ፡ መስጠት ፡ አለመስጠቱንም ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መመርመር ፡ አስፈላጊ ፡ ይመስለኛል ። የአንቀጹ ፡ አነጋገር ፡ ሚኒስትሮች ፡ በጉባኤ ፡ ተነጋግረው ፡ የሚወስኗቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በኩል ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ይቀርባሉ ፡ የሚል፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታን ፡ የያዘ ፡ ስለሆነ ፡ ድንጋጌም ፡ ሆነ ፡ ትእዛዝ ፡ አመንጭቶ ፡ ከመላክ፡ የሚከለክል ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ለመተቸት ፡ ይቻላል ። ይህ ፡ ግን ፡ በአንቀጹ ፡ ውስጥ ፡ በጉልህ ፡ የተገለጠ ፡ ሳይሆን ፡ የአንቀጹን ፡ አነጋገር ፡ በመተርጐም ፡ የሚሰነዘር ፡ አስተያየት ፡ መሆኑ ፡ መታወቅ ፡ አለበት ። እስካሁንም ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ትርጉም ፡ በመከተል ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ድንጋጌና ፡ ትእዛዝ ፡ እያመነጨ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በማቅረብ ፡ ሲፈቀድ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡እየታተመ ፡ ሲሠራበት ፡ ቆይቷል ። አሁን ፡ ግን ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፬ ፡ ይህንኑ ፡ ተግባር ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በጉልህ ፡ ሰጥቷል ። የዚህንም ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታ ፡ በሶስተኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ እገልጻለሁ ።

---

1. አንቀጽ ፡ ፸፮ ፡ ሌሎች ፡ ውሳኔዎችንም ፡ ይመለከታል ።

እንኳን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋለም ፡ ቢባልም ፡ በመሠረቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፸፩ ፡ እና ፡ ፹፮ (ሀ) ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት፡ ሳይመክርበት ፡ የሕግ ፡ ሃሳብ ፡ በቀጥታ ፡ ለፓርለማ ፡ የመላክ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቷቸው ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከርሳቸው ፡ በታች ፡ ስለ ፡ መንግሥቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ውሣኔ ፡ የመስጠቱን ፡ ሥልጣን ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሰጡበት፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፩ ፡ ከታወጀ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚመነጨው ፡ የሕግ ፡ ሃሳብ ፡ ወደ ፡ ፓርለማ ፡ ከመላኩ ፡ በፊት ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መታየት ፡ እንዳለበት ፡ ሕጉ ፡ ያስረዳል ። ይህም ፡ ቢባል ፡ የሕጉ ፡ ሃሳብ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ሳይቀበሉት ፡ ለፓርለማ ፡ ሊላክ ፡ አለመቻሉ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

፪/ እንዲሁም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፓርለማ ፡ ዝግ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ አስቸኳይ ፡ ጉዳይ ፡ ሲያጋጥም ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ የሚሠራበት ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ ድንጋጌ ፡ ለመደንገግ ፡ የሚችሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ያስረዳል ። ሆኖም ፡ እነዚህም ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚታወጁት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መክሮባቸው ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ሲፈቀዱ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለማስረዳት ፡ ድንጋጌ ፡ በሚታወጅበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በመግቢያው ፡ ላይ ፡-

> "በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ በአንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልክተን ፡ የሚኒስትሮቻችን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የመከረበትን ፡ አይተን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ድንጋጌ ፡ አውጀናል ፡" የሚሉ ፡ ቃላት ፡ መገኘታቸውን ፡ መጥቀስ ፡ ይበቃል ።

፫/ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ እና ፡ ፺፩ ፡ መሠረት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፓርለማ ፡ መክሮባቸው ፡ የሚያስተላልፋቸውን ፡ ሕጎች ፡ ያልተቀበሉአቸው ፡ እንደሆነ ፡ በዚሁ ፡ የሕግ ፡ ሃሣብ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ የሕግ ፡ ሃሣብ ፡ ጨምረው ፡ ወደ ፡ ፓርለማ ፡ መልሰው ፡ ለመላክ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በአሠራር ፡ ግን ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በዚህም ፡ ተግባር ፡ ተሳታፊ ፡ ነው ።

፬/ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ሁለት ፡ ከአንቀጽ ፡ ፷፯-፸፯ ፡ እንደተዘረዘረው ፡ የሕግ ፡ ማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡ ተገልጿል ። በነዚህ ፡ አንቀጾች ፡ መሠረት ፡ የሚታወጁ ፡ ሕጎችም ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የሚታተሙት ፡ በቅድሚያ ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እየታዩ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ሲቀበሏቸው ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚቋቋመው ፡ "የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ አቋምና፡ የሚኒስትሮችን ፡ የሥራ ፡ አኳኋን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይወስናል ፡" በሚለው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፷፯ ፡ መሠረት ፡ በሚወጣ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ። ይህም ፡ ቢሆን ፡ ጉዳዩ ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተመክሮበት ፡ የሚፈጸም ፡ ለመሆኑ ፡ በሕጉ ፡ መግቢያ ፡-

> "በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ በአንቀጽ ፡ ፷፯ ፡ የተመለከተውን ፡ እንዲሁም ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የመከረበትን ፡ አይተን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አዘናል ፡"

የሚል ፡ መሆኑን ፡ ማስታወስ ፡ ይበቃል ። በአንቀጽ ፡ ፷፱ ፡ መሠረት ፡ የሚወጡት ፡ ሕጎችም ፡ ቢሆኑ ፡ ከዚህ ፡ የተለዩ ፡ አይደሉም ። ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፸ ፡ የሚገልጸው ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ስምምነት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ስምምነቶች ፡ አንዳንዶቹ ፡ በቀጥታ ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ እንደተፈቀዱ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡

ከዚህም ፡ በቀር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ዓመታዊ ፡ በጀትና ፡ ተጨማሪ ፡ በጀት ፡ የሚመነጨው ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መሆኑ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፲፭ ፡ እና ፡ ፩፻፲፯ ፡ በግልጽ ፡ ተጠቅሷል ። ከምክትል ፡ ሚኒስትር ፡ በታች፡ ያሉት ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምንትና ፡ ሠራተኞች ፡ ሹመት ፡ የሚያገኙበት ፡ በማዕረግ፡ የሚያድጉበት ፡ ከሥራ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ የሚዘዋወሩበት ፡ ከሥራ ፡ የሚታገዱበት ፡ ሥራ ፡ የሚለቁበትና ፡ ከሥራ ፡ የሚሰናበቱበት ፡ ሁኔታ ፡ የሚወሰነውና ፡ የአስተዳደሩ ፡ ሥነ ፡ ስርዓትም ፡ የሚመራው ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አመንጭቶና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲስማሙበት ፡ በሚወጣ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ መሆኑም ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፸፯ ፡ በሚገባ ፡ ተገልጿል ። በተጨማሪም ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ አስፈላጊነቱን ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሳይስማማበትና ፡ የተስማማበትም ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ሳይታወጅ ፡ ንብረቱ ፡ የማይወሰድበት ፡ መሆኑን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፷፮ ፡ ያስረዳል ።

እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሰጣቸው ፡ ተግባሮች ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ሕግ ፡ በማመንጨትና ፡ በማውጣት ፡ ረገድ ፡ የሚፈጽመው ፡ ሥራ ፡ ሰፊ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳሉ ።

፫/ <u>በውክልና ፡ የተሰጠው ፡ ሕግ ፡ የማውጣት ፡ ተግባር</u> ፡-

ሕግ በማውጣት ፡ ረገድ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሚፈጽመው ፡ ተግባር ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተዘረዘረው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። በውክልናም ፡ የተሰጠው ፡ ተግባር ፡ አለ ።

ሀ/ <u>በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተሰጠ ፡ ውክልና</u> ፡-

ከዛሬ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ መጋቢት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. ግርማዊ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ለመላው ፡ ሕዝባቸው ፡ ባደረጉት ፡ ንግግርና ፡ እንዲሁም ፡ በማግስቱ ፡ መጋቢት ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ በወጣው ፡ ቁጥር ፡ ፵፬ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የካቢኔውን ፡ አባሎች ፡ ራሱ ፡ መርጦ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በማቅረብ ፡ ካሾመ ፡ በኋላ ፡ መንግሥቱን ፡ እንዲያቋቁም ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶታል ። ይኸው ፡ ትእዛዝ ፡ በተጨማሪ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ማለት ፡ ሚኒስትሮች ፡ በአንድነት ፡ የሚገኙበት ፡ ጉባዔ ፡ መሆኑን ፡ በማውሳት ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ለሚወስነው ፡ ውሳኔ ፡ ሁሉ ፡ ቀጥታ ፡ ኃላፊነት ፡ ያለበትና ፡ እንዲሁም ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስር ፡ ሆኖ ፡ ለመንግሥቱ ፡ አመራር ፡ ቀጥታ ፡ ኃላፊ ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጣል ። ትእዛዙ ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጠቅላላ ፡ ውሣኔ ፡ የማድረግ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶ ፡ ከፍተኛ ፡ የፖሊሲ ፡ ጉዳይ ፡ ሲያጋጥም ፡ ብቻ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በኩል ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንዲቀርብ ፡ ያሳስባል ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ በሕግ ፡ አወጣጥ ፡ ረገድ ፡ ስላለው ፡ ተግባር ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከተዘረዘረው ፡ ሌላ ፡ በተጨማሪ ፡ ምን ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ አለ ? የሚል ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ በሰፊው ፡ አስተያየት ፡ ከተረጐምነው ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ ተግባር ፡ አልጨመረም ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ቀድሞ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ን ፡ በመተርጐም ፡ ይገኝ ፡ የነበረውን ፡ ሥልጣን ፡ አሁን ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ፡ በጉልህ ፡ አብራርቶታል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ይህ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ በጉልህ ፡ ተገኝቷል ፡ የተባለው ፡ ተግባር ፡ ምንድነው ? ቢባል ፡-

፩/ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሕግ ፡ የማመንጨት ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቷል ። ሆኖም ፡ እላይ ፡ እንደገለጽኩት ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡

ሊውሉ ፡ ሲችሉ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ ፓርለማ ፡ እንዲመክርባቸው ፡ ይደረጋል ። እነዚህም ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ስምምነቶች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ በእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕጐች ፡ እንደሚሆኑ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ይገልጻል ። ይሁንና ፡ እነዚህም ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ስምምነቶች ፡ ቢሆኑ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውሉትና ፡ የበላይ ፡ ሕግነት ፡ ደረጃ ፡ የሚደርሱት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተስማምቶባቸው ፡ እንደ ፡ ጉዳዩ ፡ ሁኔታ ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ከተፈቀዱ ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ ፓርለማው ፡ መክሮባቸው ፡ በጃንሆይ ፡ ሲጸድቁ ፡ ነው ።

ለ/ <u>በንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ በፓርለማ ፡ በአንድነት ፡ (በአዋጅ) ፡</u>[2] <u>የተሰጠ ፡ ውክልና፡-</u>

በየጊዜው ፡ የሚወጡትን ፡ አዋጆች ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ ብንመለከታቸው ፡ ሕጉን ፡ በተሻለ ፡ ሁኔታ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚያስችለውን ፡ ደንብ ፡ ከአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ሚኒስትር ፡ እንዲያወጣ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሰጡ ፡ ሆነው ፡ እናገኛቸዋለን ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ይህ ፡ እያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውልበትን ፡ ሁኔታ ፡ የሚወስነው ፡ ደንብ ፡ ራሱ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እየፈቀደ ፡ እንዲያወጣ ፡ የሚባልበት ፡ ሁኔታም ፡ አለ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ደንቡን ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እየተስማማበት ፡ እንዲወጣ ፡ በሚባልበት ፡ ጊዜ ፡ ጉዳዩ ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ይቀርባል ። ነገር ፡ ግን ፡ አዋጁ ፡ የደንብ ፡ ማውጣቱን ፡ ሥልጣን ፡ ለሚኒስትሩ ፡ ወይም ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ ለሚተዳደረው ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከተው ፡ ድርጅት ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ወይም ፡ ድርጅቱ ፡ ደንቡን ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሳያቀርብ ፡ ራሱ ፡ ለማውጣት ፡ ይችላል ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ አዋጁ ፡ የደንብ ፡ ማውጣቱን ፡ ሥልጣን ፡ ለአንድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ድርጅት ፡ ቢሰጥም ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሳያየው ፡ ደንብ ፡ እንዳይወጣባቸው ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ የከለከላቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ አሉ ። ከነዚህም ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ የሚወጣው ፡ ደንብ ፡ ቀረጥን ፡ ግብርን ፡ ወይም ፡ ጠቅላላ ፡ ዋጋ ፡ የማስከፈልን ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከት ፡ ወይም ፡ ብሔራዊ ፡ መብትን ፡ የሚነካ ፡ ከሆነ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ማየት ፡ አለበት ።

፬/ <u>ሕጐች ፡ እንዴት ፡ እንደሚዘጋጁ ፡-</u>

እንግዲህ ፡ እስካሁን ፡ እንዳየነው ፡ አዋጅና ፡ ድንጋጌ ፡ በሚታወጅበት ፡ ትእዛዝና ፡ ደንብ ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሕጐቹን ፡ ረቂቆች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ የሚመለከታቸው ፡ መሆኑን ፡ ተረድተናል ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የሚቀርበው ፡ ሌላው ፡ ጥያቄ ፡ ምናልባት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ይፈጽማል ? ሕጉንስ ፡ ማነው ፡ የሚያዘጋጀው ? ለዚህስ ፡ በቂ ፡ ድርጅት ፡ አለው ፡ ወይ ? የሚል ፡ ይሆናል ። መልሱ ፡ የሚከተለው ፡ ይሆናል ። አንድ ፡ የሕግ ፡ ሃሳብ ፡ ሲመነጭ ፡ ረቂቁ ፡ ጉዳዩ ፡ በሚመለከተው ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ራሱን ፡ በቻለው ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ አማካይነት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ጉዳዩ ፡ በሚመለከተው ፡ ሚኒስቴር ፡ በኩል ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ይቀርባል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አሳቡን ፡ ብቻ ፡ አቅርቦ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሲቀበለው ፡ ሕጉ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ላቀረበው ፡ ሚኒስቴር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ይላካል ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ የተዘጋጀው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ለምክር ፡ ቤቱ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ፡

2. በዚህ ፡ ክፍል ፡ "አዋጅ ፡ " የሚለው ፡ ቃል ፡ ድንጋጌንም ፡ ይጨምራል ። ምክንያቱም ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ እንደተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ የሚሠራበት ፡ ሕግ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

ምክር ፡ ቤቱ ፡ ረቂቁ ፡ በዝርዝር ፡ እንዲጠና ፡ ለራሱ ፡ የሕግ ፡ ኰሚቴ ፡ ያስተላልፈዋል ። ለሕግ ፡ ኰሚቴውም ፡- የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፤ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማ/ጠ/መ/ ቤትና ፡ የጡረታ ፡ ድርጅት ፡ የበላይ ፡ ኮሚሺነር ፤ ከጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቀማዊ ፡ አባሎች ፡ ሲሆኑ ፡ የጉዳዩ ፡ አቅራቢ ፡ ሚኒስትር ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የኮሚቴው ፡ ሰብሳቢ ፡ ባሉበት ፡ ረቂቁ ፡ በዝርዝር ፡ ይታያል ። ኮሚቴው ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሥራውን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ወቅት ፡ ለሥራው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ማንኛውንም ፡ አገልግሎት ፡ የሚያገኘው ፡ ከአቅራቢው ፡ ሚኒስቴር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ነው ። ሕጉ ፡ እንደገና ፡ እንዲጻፍ ፡ የሚያስፈልግ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜም፣ የአቅራቢው ፡ ሚኒስቴር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ የጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ጽሕፈት፡ ቤት ፡ እንዲሠራው ፡ ይደረጋል ። ኰሚቴው ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በዝርዝር ፡ አጥንቶ ፡ የሚስማማበትም ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባዔ ፡ ይቀርባል ። የምክር ፡ ቤቱም ፡ ጉባዔ ፡ የቀረበው ፡ ሕግ ፡ የሚያከራክር ፡ ሆኖ ፡ ካገኘው ፡ በዝርዝር፡ ያየዋል ፡ ለሁሉም ፡ ተስማሚ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ የኰሚቴው ፡ ሃሳብ ፡ ይጸድቃል ። በዚህ፡ አኳኋን ፡ ያለቀለት ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ በአዋጅ ፡ መልክ ፡ የሚወጣ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴፩ ፡ መሠረት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲስማሙበት ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ በኩል ፡ ለፓርለማ ፡ ይላካል ። ረቂቁ ፡ ድንጋጌ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሆን፡ ደግሞ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴፩ ፡ እና ፡ በትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፺፬ ፡ መሠረት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀርቦ ፡ ሲፈቀድ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ እንዲታተም ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ለጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ ይላካል ። ምክር ፡ ቤቱ ፡ የተስማማበት ፡ ረቂቅ ፡ ደንብ ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ በአቅራቢው ፡ ሚኒስቴር ፡ በኩል ፡ ለጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ተልኮ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱም ፡ በበኩሉ ፡ ደንቡ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ እንዲታተም ፡ እንዲያደርግ ፡ ለጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ ያስተላልፈዋል [3] ።

ባጭሩ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሕግ ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ ተግባር ፡ ይህ ፡ ነው ።

3. ሕጉ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ እንዲታተም ፡ ለጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚላክበት ፡ ምክንያት ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ ሕጎች ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ እንዲታተሙ ፡ የሚያደርገው ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ፡ ነው ፡ ስለሚል ፡ ነው ። ሆኖም ፡ እነዚህ ፡ አዲስ ፡ የሚወጡት ፡ ሕጎች ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ታትመው ፡ ከመውጣታቸው ፡ በፊት ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ ከነርሱ ፡ በፊት ፡ ከወጡት ፡ ሕጎች ፡ ጋር ፡ የሚቃረኑ ፡ አለመሆናቸውንና ፡ ፎርማቸው ፡ ትክክል ፡ መሆኑን ፡ መርምሮ ፡ የሚያረጋግጠው ፡ የጠቅላይ ፡ ሚኒስትር፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ነው ።